# የኢትዮጵያ መንግስት ህግን የሚያስከብረው መቼ ይሆን?

## የዴሞክራሲ ለውጥ ይመጣል እያልን አንጋጠን ስንጠብቅ መንግስት ትላንትና የደርግ አገልጋዮችና በወንጀል ተከሰው የነበሩትን ከጎኑ አሰልፎ የኢትዮጵያ ህዝብን ሰላም በቂም ተበቃዮች እያተራመሰ ነው።

**ነጻ ሚድያ ነኝ በሚል ሽፋን የሚንቀሳቀሰው የግንቦት 7 ልሳን መሆኑ ከህዝብ ዓይን መሰወር ያልቻለው ኢሳት ከአሁን በፊት በትግራይ፣ሶማልያና በኦሮሞ ህዝብ በተለይ በእነ ዶ/ር ደብረጽዮን፣ ኣቶ ለማ መገርሳ፣ በዶ/ር ጸጋየ አራርሳ፣ በአቶ በቀለ ገርባ፣ በአነግና ህወሓት ታጋዮች ላይ ከፍተኛ የማጥላላትና የመነጠል ዘመቻ ላይ ተጠምዶ እንደነበርና ፌደራሊዝምን ኣፍርሶ አሃዱአዊ ስርዓት እንዲመሰረት ከፍተኛ ውዥንብር ሲበትን መቆየቱ ከህዝብ የሚሰወር አይደለም። በስመ ጸረ ወያኔ በህዝቦች ላይ ቅራኔ  እንዲነግስና በብሄር የተደራጀውን የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም እንዲጠላና እንዲፈራርስ ህቡአን አባላቱንና ታጣቂዎቹን በማሰማራት ብሄራሰቦች እርስ በርሳቸው እንዲናከሱ እያደረገ እንደሆነ በአዲስ አበባ፣ በሰሜን ጎንደር፣ በአርባ ምንጭና በድሬዳዋ ያለውን ሁኔታን በቅርብ የሚከታተል ኢትዮጵያዊ በቀላሉ ሊደርስበት ይችላል። በዚህ አላበቃም። የግለሰቦችን መልካም ስምንና ክብርን ማጉደፉ እንደ ተራ ጉዳይ ወስዶ እነሱን የሚመለከት ምንም ዜና ሳይኖር የዜጎችን ፎቶግራፍ በመለጠፍና ታሰሩ፣ ዘረፉ ወዘተ የሚል ርእስ በመስጠት የዜጎችን መልካም ስማ  ከማጉደፉም በላይ በቤተሰብ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤዎች እየፈጠረ ነው። ይህን በግልጽ ለመረዳት ቀጥሎ ያሰፈርኩትን እንደአብነት መመልከት ይቻላል። ይህ ተግባር በህዝብ ላይ የሚደረግ ወንጀል [PUBLIC OFFENCE] ስለሆነ በመንግስት ጠበቃ የሚያዝ ጉዳይ ነው። መንግስት የተጠቂዎችን መልካም ስም እንዲመለስ፣ ኢሳት ላደረሰው ጉዳት ካሳ እንዲያገኙ ማድረግና አጥፊውን እሳት በህግ በመቅጣት ሌሎችም እንዲማሩበት መድረግ ይጠበቅበታል።**

## የኢትዮጵያ መንግስት ሆይ! “ ህግ ያልገዛው ነጻነት ሃይል ይገዛዋል” የሚል ምሳሌ ሳይደርስብን ስራህን ስራ!

## ጋጠወጦችን ተቆጣጠርልን!

https://www.youtube.com/watch?v=BA0cYbz2mug




**ብዙ ወንጀሎች አዜብ መስፍን በዘርፈ ብዙ ወንጀሎች ተጠርጥራ በዛሬው እለት በቁጥጥር ዋለች | bereket simon & TPLF**

**ተክለሃይማኖት ነኝ**